የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፸
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No.70
ADDIS ABABA, 28th August, 2015

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፵፭/፪ሺ፯ ዓ.ም

የጢያ ትክል ድንጋዮች ዓለም አቀፍ ቅርስ የተከለሉ ሥፍራዎችን ለመሰየም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ............ገጽ ፰ሺ፫፻፷፮

አባሪ............ገጽ ፰ሺ፫፻፸፬

CONTENTS

Regulation No.345 /2015

Tiya Carved Standing Stones World Heritage Reserved Area Designation Council of Ministers Regulation......Page 8366

Annex............Page 8374

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፭/፪ሺ፯

**የጢያ ትክል ድንጋዮች ዓለም አቀፍ ቅርስ የተከለሉ ሥፍራዎችን ለመሰየም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪" አንቀጽ ፭ እና ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፱/፲፱፻፺፪ አንቀጽ ፵፪(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የጢያ ትክል ድንጋዮች ዓለም አቀፍ ቅርስ የተከለሉ ሥፍራዎችን መሰየሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፭/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

Council of Ministers Regulation No. 345/2015

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE DESIGNATION OF TIYA CARVED STANDING STONES WORLD HERITAGE RESERVED AREA**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 42(1) of the Research and Conservation of Cultural Heritage Proclamation No. 209/2000.

**PART ONE**

**GENERAL**

1. **Short Title**

This regulation may be cited as the "Tiya Carved Standing Stones World Heritage Reserved Area Designation Council of Ministers Regulation No. 345/2015"

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 19.75

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩/ "አዋጅ" ማለት ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ የወጣው አዋጅ ቁጥር ፪፻፱/፲፱፻፺፪ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፫ የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፫/ "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፪፻፱/፲፱፻፺፪ የተቋቋመው የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

፬/ "እምብርት ዞን" ማለት መካነ-ቅርሱ በዓለም-አቀፍ ቅርስነት የተመዘገበበትን የላቀ ሁለንተናዊ እሴት የያዘው የቅርሱ ይዞታ የሚገኝበት ስፍራ ሆኖ፣ የቅርሱን ጥንታዊ ይዘት እና ሙልዕነት የሚያሳየው እና መካነ-ቅርሱን ለመጠበቅና ለማስተዳደር የሚረዱ ሥራዎች ብቻ የሚከናወኑበት የቅርሱ ክልል ነው፤

፭/ "ደጀን ዞን" ማለት ለተመዘገበው መካነ-ቅርስ ተጨማሪ ጥበቃ ለማድረግ እንዲቻል በእምብርት ዞኑ ዙሪያ የሚከለል አዋሳኝ ስፍራ ሲሆን፣ በዚህ ስፍራ የሚኖረውን የመሬት አጠቃቀም እና የልማት ሥራዎች ለመወሰን የሚያስችል ድንጋጌ የወጣለት እና ቅርሱ ከአካባቢው ጋር የሚኖረውን የእይታና መልክዓ-ምድራዊ ትስስር ለመጠበቅ ታስቦ የሚከለል ስፍራ ነው፤

፮/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፯/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

## 2. Definitions

In this regulation unless the context requires otherwise:

1/ "Proclamation" means the Research and Conservation of Cultural Heritage Proclamation No. 209/2000;

2/ definitions provided for under Article 3 of the Proclamation shall be applicable;

3/ "Authority" means the Authority for Research and Conservation of Cultural Heritage established under Proclamation No. 209/2000;

4/ "Core Zone" means an area that demonstrates the Outstanding Universal Value of the site, for which the heritage is included in the World Heritage List, and other important features that illustrate the integrity and authenticity that contribute for the protection and management of the heritage;

5/ "Buffer Zone" means an area surrounding the heritage which was complementary legal and/or customary restrictions placed on its use and development to give an added layer of protection to the property and includes the immediate setting of the nominated heritage, important views and other attributes that are functionally important as a support to the property and its protection;

6/ "person" means any natural or juridical person;

7/ any expression in the masculine gender includes the feminine gender.

## ክፍል ሁለት

## የጢያ ትክል ድንጋዮች ዓለም አቀፍ ቅርስ የተከለሉ ሥፍራዎች

**፫. የተከለሉ ሥፍራዎችን ስለመሰየም**

የጢያ ትክል ድንጋዮች ዓለም አቀፍ ቅርስ ቦታ እምብርትና ደጀን ዞኖች በዚህ ደንብ ተሰይመዋል።

**፬. የቅርስ ቦታዎች እምብርት ዞን**

የጢያ ትክል ድንጋዮች ዓለም አቀፍ ቅርስ ቦታ እምብርት ዞን ስፋቱ 4.47 ሄክታር ሆኖ፣

፩/ በ$8^0$ 25′ 58.4″ ሰሜን ላቲትዩድ እና $38^0$ 36 ′35.75″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፪/ በ$8^0$ 25′ 58.01″ ሰሜን ላቲትዩድ እና $38^0$ 36′ 36.25″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፫/ በ$8^0$ 25′ 58.3″ ሰሜን ላቲትዩድ እና $38^0$ 36′ 35.95″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፬/ በ$8^0$ 25′ 52.46″ ሰሜን ላቲትዩድ እና $38^0$ 36′ 41.26″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፭/ በ$8^0$ 25′ 48.61″ ሰሜን ላቲትዩድ እና $38^0$ 36′ 37.33″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፮/ በ$8^0$ 25′ 53.94″ ሰሜን ላቲትዩድ እና $38^0$ 36′ 33.05″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

መካከል ያለውን ሥፍራ ያካትታል።

**፭. የቅርስ ቦታው ደጀን ዞን**

የጢያ ትክል ድንጋዮች ዓለም አቀፍ ቅርስ ቦታ ደጀን ዞን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ የተመለከተው እምብርት ዞን ዙሪያ የሚያካልል ሆኖ፣

፩/ በ$8^0$ 26′ 3.44″ ሰሜን ላቲትዩድ እና $38^0$ 36 ′33.26″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፪/ በ$8^0$ 25′ 58.33″ ሰሜን ላቲትዩድ እና $38^0$ 36′ 29.99″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፫/ በ$8^0$ 25′ 50.34″ ሰሜን ላቲትዩድ እና $38^0$ 36′ 32.04″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

## PART TWO

## RESERVED AREAS OF TIYA CARVED STANDING STONES WORLD HERITAGE SITE

**3. Designation of Reserved Areas**

The Core and Buffer Zones of Tiya Carved Standing Stones World Heritage Site are hereby designated.

**4. Core Zones of the Reserved Area**

The Core Zone of Tiya Carved Standing Stones World Heritage site covers 4.47 hectares including the Area between:

1/ $8^0$ 25’ 58.4" Latitude North and $38^0$ 36’ 35.75" Longitude East;

2/ $8^0$ 25’ 58.01" Latitude North and $38^0$ 36’ 36.25" Longitude East;

3/ $8^0$ 25’ 58.3" Latitude North and $38^0$ 36’ 35.95 Longitude East;

4/ $8^0$ 25’ 52.46" Latitude North and $38^0$ 36’ 41.26" Longitude East;

5/ $8^0$ 25’ 48.61" Latitude North and $38^0$ 36’ 37.33" Longitude East; and

6/ $8^0$ 25’ 53.94" Latitude North and $38^0$ 36’ 33.05" Longitude East.

**5. Buffer Zones of the Reserved Area**

The Buffer Zone of the Tiya Carved Standing Stones World Heritage Site encompasses the area surrounding the Core Zone referred to in Article 4 of this Regulation and stretches between:

1/ $8^0$ 26’ 3.44" Latitude North and $38^0$ 36’ 33.26" Longitude East;

2/ $8^0$ 25’ 58.33" Latitude North and $38^0$ 36’ 29.99" Longitude East;

3/ $8^0$ 25’ 50.34" Latitude North and $38^0$ 36’ 32.04" Longitude East;

፬/ በ8⁰ 25′ 45.91″ ሰሜን ላቲትዩድ እና 38⁰ 36′ 34.74″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፭/ በ8⁰ 25′ 43.5″ ሰሜን ላቲትዩድ እና 38⁰ 36′ 37.87″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፮/ በ8⁰ 25′ 48.86″ ሰሜን ላቲትዩድ እና 38⁰ 36′ 42.48″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፯/ በ8⁰ 25′ 53.4″ ሰሜን ላቲትዩድ እና 38⁰ 36′ 44.46″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፰/ በ8⁰ 25′ 55.09″ ሰሜን ላቲትዩድ እና 38⁰36′ 44.32″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፱/ በ8⁰ 25′ 56.89″ሰሜን ላቲትዩድ እና 38⁰ 36′ 43.63″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፲/ በ8⁰ 25′ 59.81″ሰሜን ላቲትዩድ እና 38⁰ 36′ 42.48″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፲፩/ በ8⁰ 26′ 1.64″ ሰሜን ላቲትዩድ እና 38⁰ 36′ 39.89″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

፲፪/ በ8⁰ 25′ 59.99″ ሰሜን ላቲትዩድ እና 38⁰ 36′ 38.45″ ምሥራቅ ሎንግትዩድ፣

መካከል ያለውን ሥፍራ ያካትታል።

## ክፍል ሦስት

## የጢያ ትክል ድንጋዮች ዓለም አቀፍ ቅርስ ክልል ስፍራ አስተዳደር

### ፮.ስለክልል ሥፍራው አስተዳደር

፩/ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ ፭ መሠረት በጢያ ከተማ ውስጥ በሚያደራጀው የመካነ ቅርስ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ክልል ሥፍራውን ያለማ፣ ያስተዳድራል፣ ሕገወጥ ተግባራት እንዳይፈፀሙበት ይከላከላል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጢያ ዓለም አቀፍ ቅርሶች የክለላ ሥፍራ አማካሪ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

4/ 8⁰25’45.91" Latitude North and 38⁰36’34.74" Longitude East;

5/ 8⁰ 25’ 43.5" Latitude North and 38⁰ 36’ 37.87" Longitude East;

6/ 8⁰ 25’ 48.86" Latitude North and 38⁰ 36’ 42.48" Longitude East;

7/ 8⁰ 25’ 53.4" Latitude North and 38⁰ 36’ 44.46" Longitude East;

8/ 8⁰ 25’ 55.09" Latitude North and 38⁰ 36’ 44.32" Longitude East;

9/ 8⁰ 25’ 56.89" Latitude North and 38⁰ 36’ 43.63" Longitude East;

10/ 8⁰ 25’ 59.81" Latitude North and 38⁰ 36’ 42.48" Longitude East;

11/ 8⁰ 26’ 1.64" Latitude North and 38⁰ 36’ 39.89" Longitude East; and

12/ 8⁰ 25’ 59.99" Latitude North and 38⁰ 36’ 38.45" Longitude East.

## PART THREE

## ADMINISTRATION OF THE TIYA CARVED STANDING STONES WORLD HERITAGE RESERVED AREA

### 6. Administration of the Reserved Area

1/ The Authority shall develop, administer and protect the designated heritage site from illegal acts through the site management office to be organized at Tiya city pursuant to Article 5 of the Proclamation.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article an Advisory Committee to the designated heritage site (hereinafter the “Committee”) is hereby established.

## ፯· የኮሚቴው አባላት

፩/ ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

ሀ) የሶዶ ወረዳ አስተዳደር ኃላፊ......ሰብሳቢ

ለ)የጢያ ከተማ አስተዳደር ተወካይ.አባል

ሐ) የሶዶ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ..................................አባል

መ)የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ አገልግሎት ኃላፊ......................አባል

ሠ) የሶዶ ወረዳ የሃይማኖት ተቋማት ተወካዮች...............................አባላት

ረ) የሶዶ አካባቢ የሀገር ሽማግሌዎችና ታዋቂ ግለሰቦች ሁለት ተወካዮች ...............................................አባላት

ሰ) የሶዶ ወረዳ የሴቶችና ወጣቶች ማህበራት ሁለት ተወካዮች.........አባል

ሸ) የሶዶ ወረዳ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተወካይ.............አባል

ቀ) የመካነ ቅርሱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ...........................አባልና ፀሐፊ

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች አካላትንም በስብሰባው እንዲሳተፉ ሊፈቅድ ይችላል።

## ፰. የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባሮች

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩/ በጢያ ትክል ድንጋዮች ዓለም አቀፍ ቅርስ አካባቢ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባለቤትነት ተሰምቷቸው በቅርስ አጠባበቅ ላይ የጐላ ተሳትፎ ስለሚያደርጉበትና ከአካባቢው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅትና ትስስር ስለሚፈጠርበት አግባብ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

## 7. Members of the Committee

1/ The Committee shall have the following members:

a) Sodo Woreda Administrator ……chairperson

b) Representative of Tiya Town Administration........…………..……. …..member

c) Head of the Sodo Woreda Tourism and Culture Office ………………………member

d) Head of Welkite University Community Service……………………………..member

e) Representatives from each religious institutions In Sodo Woreda ……...members

f) Two Representatives of of Elders and/or Renowned people from the Sodo Woreda…………………………members

g) Two representatives of Women and Youth Associations in the Sodo Woreda……………………………members

h) Representative of Sodo Woreda Tourist Service Delivering Institutions..…..member

i) Site manager…………..member and secretary

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article the Committee, as may be necessary, allow other bodies to attend the meetings.

## 8. Power and Duties of the Committee

The Committee shall have the powers and duties to:

1/ facilitate conditions to develop sense of ownership among the local population surrounding the heritage sites to play active role in the protection of the Heritage and as to the creation of strong coordination and linkage between stakeholders of the surrounding area;

፪/ የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ እቅድ እና የእቅድ ክንውን ይገመግማል፤ ለባለሥልጣኑ ከመቅረቡ በፊት መርምሮ የማሻሻያ አስተያየት ይሰጣል፤

፫/ ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችሉት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ ሃሳብ ያቀርባል።

**፱. <u>የኮሚቴው ስብሰባ</u>**

፩/ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባውን በሦስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

፪/ ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

፫/ የኮሚቴው ውሳኔዎች በስብሰባው በተገኙ አባላት በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፲. <u>ክልከላ</u>**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፵፪(፪) የተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ፤ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ በተመለከቱት እምብርት ዞኖች ውስጥ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው፤

ሀ) በቅርሶቹ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ኬሚካሎችንና ከፍተኛ ጨረር አመንጪ መሣሪያዎችን መጠቀም፤



2/ review the annual plans and performance of the office before they are being submitted to the Authority;

3/ deliberate and forward proposals on such other issues to enable the Office to properly discharge its responsibilities.

**9. <u>Committee Meetings</u>**

1/ The Committee shall meet once in every three months; provided, however, that an extra-ordinary meeting of the Committee may be held at any time whenever called by the Chairperson.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members are present at any meeting of the Committee.

3/ Decisions of the Committee shall be passed by a majority vote; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Committee may adopt its own rules of procedure.

## <u>PART FOUR</u>

## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

**10. <u>Prohibition</u>**

1/ In addition to the prohibited activities provided under Article 42(2) of the Proclamation, carrying out the following activities within the Core Zone shall also be prohibited:

a) using chemicals and high radiation tools that can cause damage to the heritages;

ለ) ጥናትና ምርምርን ጨምሮ ማንኛውንም በባለሥልጣኑ ያልተፈቀደ ሥራ ማከናወን፡፡

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፵፪(፪) የተመለከቱት የተከለከሉ ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ፤ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ በተመለከቱት ደጀን ዞኖች ውስጥ በባለሥልጣኑ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖር የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን የተከለከለ ነው፤

ሀ) የቅርሱን የእይታ ትስስር እና የላቀ ሁለንተናዊ እሴት የሚጎዳ የህንፃ ግንባታ፤

ለ) ከፍተኛ ኃይል ተሸካሚና አስተላላፊ የኤሌክትሪክና የስልክ ምሰሦዎች ተከላ፤

ሐ) የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖች ግንባታ፤

መ) የማዕድን ማውጣትና ቁፋሮዎች፤

ሠ) በቅርሶቹ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ዛፎችን መትከል፤

፲፩. **<u>የባለሥልጣኑን ፈቃድ ስለማግኘት</u>**

በደጀን ዞኖች ውስጥ የሚፈቀዱ ተግባራትን ለማከናወን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑን ማማከርና ይሁንታ ማግኘት አለበት፡፡

፲፪. **<u>አስተዳደራዊ መቀጫ</u>**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ የተከለከሉትን ተግባራት በመተላለፍ በቅርሶችና በቅርስ ክለላ ስፍራዎች ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ በደረሰው ጉዳት ልክ አስተዳደራዊ መቀጫ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፲፫. **<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከጽህፈት ቤቱ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

b) carrying out any activity which is not authorized by the Authority.

2/ In addition to the prohibited activities provided under Article 42(2) of the Proclamation carrying out the following activities within the Buffer Zone without the authorization of the Authority shall also be prohibited:

a) construction of buildings affecting the visual integrity and Outstanding Universal value of the heritage site;

b) installation of high tension electric and telephone transmission towers;

c) construction of water reservoirs;

d) mining and quarrying activists;

(e) planting trees that can cause damage to the Heritage.

11. **<u>Consulting and Getting Approval from the Authority</u>**

Any person who intends to carry out activities permitted within the Buffer Zone shall consult and get approval of the Authority.

12. **<u>Administrative Penalty</u>**

Whosoever causes damage to heritages or the reserved heritage area in contravention of Article 10 of this Regulation, without prejudice to the punishments provided for in the other relevant laws, shall be subject to administrative penalty equivalent to damage sustained.

13. **<u>Duty to Cooperate</u>**

Any person shall have duty to cooperate with the Office for the implementation of this Regulation.

፲፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**


**14. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.


**Done at Addis Ababa, this 28th day of August 2015**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**


## አባሪ ፩ Annex 1


ሶዶ ወረዳ
SODO WEREDA
የ ጢያ ዓለም - አቀፍ ቅርስ
THE TIYA WORLD HERITAGE SITE
Legend
TIYA WORLD HERITAGE SITE
SODDO_WEREDA
የ ደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል
SOUTHERN NATION NATIONALITIES AND PEOPLES REGION
SODO WEREDA
Gurage
Legend
MAP OF ETHIOPIA
SOUTHERN NATION NATIONALITIES
Meters
0137,500275,000 550,000 825,000 1,100,000

## አባሪ ፪ Annex 2



የ ጢያ ዓለም - አቀፍ ቅርስ
TIYA WORLD HERITAGE SITE
456800
457000
457200
457400
457600
457800
931700
931800
931900
932000
932100
932200
932300
N
W
E
S
Legend
BUFFER ZONE
CORE ZONE
Meters

የ ሶዶ ወረዳ እና የ ጢያ ዓለም - አቀፍ ቅርስ
TIYA WORLD HERITAGE SITE IN SODO WEREDA
457000
458000
932000
932700
SODO WEREDA
Gurage
N
W
E
S
Legend
BUFFER ZONE
CORE ZONE
CONTOUR
MAJOR ROAD
SODO WEREDA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት